


# +++ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ +++

# የዕለት እንጀራ

ሚያዝያ ፰ **ማቴዎስ ፳፩፡ ፲፰-፳፪** ፳፻፩




ይህ የዐቢይ ጾም የመጨረሻው ሳምንት ሰሙነ ሕማማት ይባላል። ይህም ዓለምን ለማዳን ሲል ጌታችንና አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ታላቅ መከራ (ሕማም) መቀበሉን የምናስብበት ነው።

እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ።
ኢሳ ፶፫: ፭

በማለዳም ወደ ከተማ ሲመለስ ተራበ።
በመንገድም አጠገብ በለስ አይቶ ወደ እርስዋ መጣ፤ ከቅጠልም ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና። ለዘላለሙ ፍሬ አይገኝብሽ አላት። በለሲቱም ያንጊዜውን ደረቀች።
ደቀ መዛሙርቱም ይህን አይተው። በለሲቱ ያንጊዜውን እንዴት ደረቀች? ብለው ተደነቁ።
ኢየሱስም መልሶ:- እውነት እላችኋለሁ፥ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩም፥ በበለሲቱ እንደ ሆነባት ብቻ አታደርጉም፤ ነገር ግን ይህን ተራራ እንኳ። ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ብትሉት ይሆናል፤ አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ አላቸው።

የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።
ኢሳ ፶፫: ፭

## በሰሙነ ሕማማት በዚህ ዕለት የሚታሰበው፡

**ስለዓለም መዳን የተሰቀለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከበለስ ፍሬ ፈልጎ አጣ**

| መከራውን ከሚናገሩትና የስቅለት ቀን በዜማ ከሚዜሙት መካከል | ትርጉም |
|---|---|
| ተንሥኡ ላ'ዕሌየ ሰማዕተ ዐመፃ<br>ወዘኢየአምር ነበቡ ላዕሌየ<br>ተንሥኡ ላዕሌየ ሰማዕተ ዕመፃ | የዓመፅ ምስክሮች ተነሡብኝ<br>የማላውቀውንም በእኔ ላይ ተናገሩ<br>የዓመፅ ምስክሮች ተነሡብኝ |